# መንግስት የሰላማዊውን ሙስሊም መብት ለምን አያስከብርም?

## ❖ እስከመቼ አርብ በመጣ ቁጥር ፀሎታችን በሁከት ይስተጓጎላል?

ጀማል ኑሩ 08/05/13

በመዲናችን አዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች 'ጥያቄያችን ሃይማኖታዊ ነው፣ በህግ ጥላ ስር የሚገኙ ግለሰቦች ይፈቱ' የሚሉ ጥቂት አክራሪዎች ሁከትንና ብጥብጥን በማለም በምንስግድባቸው የተለያዩ መስጂዶች ውስጥ እየገቡ ለአላህ ፀሎት የምናደርስበት ቦታ ያሳጡን መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። እነዚህ አክራሪዎች በተለይም በቅርቡ በታላቁ አንዋር እና በቤኒን መስጂዶች ውስጥ ባካሄዱቸው ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች ምንም እንኳን የህይወት መጥፋት አደጋ ባይከተልም፣ ቀላል የማይባል ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳት ማድረሳቸው ግን የሚዘነጋ አይደለም።

ምንም እንኳን ሁከቱ ተጨማሪ ጉዳት ሳያስከትልና ሳይስፋፋ በአጭሩ የተቀጨ ቢሆንም፤ ክስተቱን ተከትሎ ከተለያዩ ወገኖች የሚሰነዘሩ አስተያየቶችና መላ-ምቶች በስፋት ሲደመጡ ሰንብተዋል። የአመፁ ተዋንያን ናቸው ተብለው ከተፈረጁት ጥቂት አክራሪዎች ጀምሮ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ስለሁኔታው ከየራሳቸው ፍላጎት በመነሳት አስተያየት የሰጡ ሲሆን፤ በመንግስት በኩልም ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የተሰጠ መግለጫ ነበር–መንግስት ከእንግዲህ ወዲህ ትዕግስቱ በመሟጠጡ ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስድ የሚያሳስብ። ይህን ሁኔታን ተከትሎም በሰላም ወዳዱ ህብረተሰብ በተለይም በአብዛኛው ሰላም ወዳድ ሙስሊም ዘንድ እነዚህን ፅንፈኞች የሚያወግዙ የተቃውሞ ሰልፎችም እንደቀጠሉ ናቸው።

ታዲያ እዚህ ላይ 'የሁከቱ መንስኤ ምንድነው? ሁከት ፈጣሪዎቹ እነማን ናቸው? እና ሁኔታው በአሁኑ ወቅት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?' የሚሉ ጥያቄዎችን በዋነኛነት ማንሳት ያስፈልጋል። ይሁንና ጥያቄዎቹን ለመመለስ እኔም እንደ አንድ ሙስሊም ዜጋ 'መንግስት የሰላማዊውን ሙስሊም መብት ለምን አያስከብርም?፣ መጅሊሱስ ምን እየሰራ ነው? እንዲሁም እስከመቼ አርብ በመጣ ቁጥር ከፀሎታችን በሁከት እንስተጓጎላለን?'

የተሰኙ ጥያቄዎችን ማቅረብ እፈልጋለሁ—እንደ አንድ ሙስሊም ዜጋ ምላሹን ከመንግስትና ከመጅሊስ በመሻት።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የአንድ አሊያም የጥቂት እምነት ተከታዮች ሀገር አይደለችም። ማንኛውም ዜጋ የፈለገውን ኃይማኖት በእኩልነትና በነፃነት የማምለክ ህገ - መንግስታዊ ዋስትና ተሰጥቶታል። በመሆኑም የትኛውም ዜጋ በአምልኮው የተነሳ የሚደርስበት ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የለም። አንዱ ኃይማኖት ሌላውን ማንቋሸሽ፣ መቃወም አሊያም ከሌሎች እኩይ ዓላማዎች ተነስቶ ተፅእኖ ማሳረፍ፣ ማበጣበጥ፣ ማሳደድ፣ መግደልና መሰል ተግባራትን መፈፀም አይችልም። እርግጥ ይህን መሰሉ ድርጊት በታሪካችን ታየቶም ሆነ ተሰምቶ አይታወቅም። ምክንያቱም ሀገራችን ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ ከምትታወቅባቸው መልካም እሴቶቿ ውስጥ አንዱ ጉዳይ በርካታ ሃይማኖቶች ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩባት ምድር መሆኗ ነው።

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀውና በኢፌዴሪ ህገ - መንግስት አንቀፅ 11 ላይ በግልፅ እንደተደነገገው፤ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው። መንግስት በማንኛውም ሃይማኖታዊ ስርዓት ውስጥ እጁን አስገብቶ "እንዲህ መደረግ አለበት፤ ይህ ደግሞ መከናወን የለበትም…" እያለ የሚወስንበት ጉዳይ የለም፤ ኖሮም አያውቅም፤ ወደፊትም አይኖርም። ሃይማኖቶችም ቢሆኑ እንዲሁ። በሃይማኖትና በፖለቲካ መካከል ግልፅ ልዩነትን ያበጀው ይህ ህገ- መንግስታዊ ድንጋጌ፤ በግልፅም ሆነ በስውር ሃይማኖት የፖለቲካ አጀንዳ ማራማጃ መሆን እንደማይገባው ያመላክታል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው ትልቁ ጉዳይ፤ መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ ናቸው ሲባል ማናቸውም የእምነት ተቋማት አሊያም ተከታዮች በሃይማኖት ሽፋን የሃገሪቱን ህግ የሚጥስ ተግባር መፈፀም ይችላሉ ማለት አለመሆኑን ነው።

እናም የኃይማኖት ተቋማትም ሆኑ ተከታዮቻቸው ኃይማኖታዊ ስርዓታቸውን ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መልኩ መፈፀም ይኖርባቸዋል። ጥያቄ ቢኖራቸው እንኳን ህግና ስርዓትን ተከትለው ማቅረብ ይኖርባቸዋል እንጂ፣ ከመሬት ተነስቶና ውሃ በማይቋጥር እሳቤ ለአመፅና ለብጥብጥ መጋበዝ ከሀገሪቱ ህግ ጋር መላተምን ስለሚያስከትል አግባብነት የለውም። ሁላችንም እንደምናውቀው የትኛውም ሃይማኖት ሰላምን እንጂ ሁከትን አይሰብክም፤ አይፈቅድምም። ታዲያ ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሃይማኖትን ሽፋን

በማድረግ በማንኛውም ሁኔታ ለአመፅና ለግርግር የሚነሳሳ ኃይል ካለ፣ ጉዳዩ ሃይማኖታዊ ሳይሆን የሀገርንና የሕዝብን ሰላም በማወክ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መሆኑ እርግጥ ነው። በመሆኑም መንግስት ይህን መሰሉን ተግባር እያየ በዝምታ ማለፍ ያለበት አይመስለኝም– የሀገርን ሰላም የሚያደፈርሱ ብሎም የአብዛኛውን ሙስሊም የሃይማኖትና የአምልኮ ነፃነትን የሚደፈጥጡ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ተግባራቱን ፈር የማስያዝ ግዴታ አለበትና።

ለመሆኑ በሀገራችን የኃይማኖት ነፃነትና እኩልነት እንዳለ በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር ተፈፃሚ እየሆነ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ በቅርቡ በሃይማኖት ሽፋን የተቃጣው ፖለቲካዊ የአመፅ እንቅስቃሴ ከቶ ከምን ሊመነጭ ይችላል?– ይህ መነሳት ያለበት ወቅታዊ ጥያቄ ይመስለኛል። ታዲያ ለዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ “ወሐቢይ/ሰለፊ” በሚል ሃይማኖት ሽፋን በውጭ ሃይሎች ምንዳ የተደራጀውን ሃይል የኋላ አመጣጥን በጥቂቱም ቢሆን መመልከት ያስፈልጋል። እንደሚታወቀው የእስልምና እምነት በሀገራችን የነበረ፣ ያለና ለወደፊትም የሚኖር ሃይማኖት ነው። የሃይማኖቱ ተከታዮችም ብንሆን እርስ በርሳችን ብቻ ሳይሆን፤ ከሌሎች እምነት ተከታይ ወንድሞቻችን ጋር ተከባብረንና ተቻችለን ለዘመናት ኖረናል፤ ወደፊትም አብረን እንኖራለን።

ሆኖም ይህ ነባራዊ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከቅርብ አመታት ወዲህ ግን ለአክራሪነት ክስተት መንስኤ የሆኑ ቡድኖች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ማቆጥቆጣቸው አልቀረም። እነዚህ ቡድኖች ሲነሱ ሃይማኖታዊ አላማን የሰነቁ መስለው ቢሆንም፤ ከበስተጀርባቸው ግን ሌላ አጀንዳን የማራመድ ዕቅድ ነበራቸው። ይሁንና በሃይማኖት ሽፋን ለማራመድ ያሰቡትን ሴራ ገሃድ እስካላወጡና ሌላ ጉዳት እስካላስከተሉ ድረስ ማንም እውቅና ሊነፍጋቸው አይችልም። ምክንያቱም በሰላማዊ መንገድ ሃይማኖታዊ ስርአታቸውን የማካሄድ ህገ- መንግስታዊ መብትና ነፃነት ያላቸው ስለሆነ ያለምንም ተፅእኖ ለመደራጀት ችለዋል፤ ለጥቂት ጊዜያትም ቢሆን ሰላማዊ መስለው ለመታየት ሞክረውም ነበር።

ዳሩ ግን እነዚህ ሃይሎች ድብቁን አጀንዳቸውን ሸሽገው መቆየታቸው ከጀርባቸው ሆነው “በዚህ ግቡ፤ በዚህ ውጡ” እያሉ እንዳሻቸው ከሚያሽከረክሯቸው የውጭ አክራሪ

ቡድኖች የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ የሚያሳጣቸውና ወደ መጥፋት የሚያሸጋግራቸው መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ውስጥ ውስጡንም ቢሆን እኩይ ተግባራቸውን መፈፀም ነበረባቸውና እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉ። እናም የአመፃ እርምጃቸውን ለዘመናት በፍቅርና በአንድነት በኖረው የሙስሊሙ ህዝብ ላይ ነበር በቅድሚያ መተግበር የጀመሩት።

እነዚህ ኃይሎች የተደራጁበት ዓላማ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ገና በለጋ የሁከት ዕድሜያቸው በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ በሚያራምዱት አፍራሽ ተግባር አረጋግጠዋል። ለዚህም የሙስሊሙ ማህበረሰብ አኩሪ እሴቶችን ለማጥፋት ያደረጉት ርብርብ አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው። የእምነቱ ተከታዮች ለድሃ የምንመፀውትበት የ'ሰደቃ' ስርዓት እንዳይፈፀም ማድረግ፣ የመቃብር ስፍራዎችን በማፍረስ ሙስሊሞች ኃይማኖታዊ ስርዓታችንን ጠብቀን ቀብር እንዳናካሂድ መከልከል፣ የሃይማኖቱ መሪዎችን /ኢማሞችን/ ማሳደድና መግደል፣...ወዘተርፈ ካደረጓቸው እንቅስቃሴዎችና የእምነቱን እሴቶች ለማጥፋት ካካሄዷቸው ዘመቻዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ፍቅርና አንድነት እንዳይኖር ያካሄዷቸው ዘመቻዎች እንደነበሩም የሚካድ አይደለም። በሰበብ አስባቡ ሙስሊሙ ህዝብ እርስ በርሱ እንዲበጣበጥ፣ ከሌላ ሃይማኖት ተከታይ ወንድሞቹ ጋርም አብሮ ተከባብሮና ተቻችሎ እንዳይኖር አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ጥረዋል፤ ግረዋል–ሴራን እንደተቀደሰ ተግባር በመቁጠር። ያለአንዳች ተጨባጭ ምክንያትም ህዝበ-ሙስሊሙን "መንግስት በሃይማኖትህ ውስጥ ጣልቃ ገብቷል" እያሉ ሲሰብኩ መኖራቸውም ከማንም የተሰወረ ሃቅ አይደለም። በዚህም አብዛኛው ሙስሊም ህዝብ በምንሰግድባቸው መስጂዶች ውሰጥ ሰላማችንን አጥተናል፤ መብታችንንም ተነፍገናል፤ተነጥቀናልም።

ያም ሆኖ ግን የእነዚህ ሃይሎች ፍላጎት ፈፅሞ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ከሰላማዊው የእምነቱ ተከታይ የተሰወረ አልነበረም። በመሆኑም ህዝበ- ሙስሊሙ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን እንዲሁም ከሰላም ይልቅ ሁከትን የሚሰብከውን የቡድኑን የዘወትር ውትወታ ሊቀበለው አልፈቀደም። ቡድኑ ካለው እድሜና ካካሄደው ሰፊ የቅስቀሳ ዘመቻ አንፃር ፋይዳ ያለው ነገር ያለማድረጉና በጥቂት ተከታዮች ብቻ ተወስኖ የመቆየቱ ምስጢር ይኸው መሆኑን ስለሚገነዘብም ምግባራቸውን እየኮነነው ይገኛል። እናም የአክራሪው ቡድን

ነገረ-ስራ በትክክለኛ ሃይማኖታዊ መሰረት ላይ የተገነባ ባለመሆኑ በአብዛኛው ሰላም ወዳድ ሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት አጥቷል። ግና እነዚህ ኃይሎች ፍላጎታቸው ሌላ ነበርና ከተያያዙት አፍራሽ ተልዕኮ ሊታቀቡና ወደ ትክክለኛው ጎዳና ሊመለሱ አልቻሉም። ይልቁንም ተቀባይነት ማጣታቸው ይበልጥ ተስፋ እያስቆረጣቸውና እንቅስቃሴያቸውም ሃይል የተሞላበት ሆኖ ነው የቀጠለው። ለዚህ አባባሌ በቅርቡ በደሴ ከተማ ሸዋ በር መስጂድ ኢማም የነበሩትን ሼህ ኑር ይማምን በሚዘገንን ሁኔታ መግደላቸውና ኋላ ላይም ያለ አንዳች ሐፍረት ግድያውን "ድራማ ነው" ማለታቸውን አስረጅ አድርጌ ማቅረብ እችላለሁ። አዎ! ነገረ-ስራቸው "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል" እንዲሉት ነውና።

ያም ሆነ ይህ ግን እነዚህ ሃይሎች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ የጀመሩትን አፍራሽ እንቅስቃሴ በመያዝ መንግስት በሐሰት ለመወንጀል ጥረት ከማድረግ ወደኋላ አላሉም። "ጥያቄ አለን፣ ተገቢው ምላሽ ይሰጠን" በሚል ከመንግስት ጋር ተደጋጋሚ ሙግት ሲገጥሙ ቆይተዋል። ይህን በሚያደርጉበት ወቅት ግን ከመንግስት በኩል የገጠማቸው እንዳሰቡት የ"እንካ ሰላንቲያ" ዓይነት ሁኔታ ሳይሆን በሰከነና በረጋ መንገድ መፍትሔ የመሻት ጉዳይ ነበር። ይህ የሆነው ደግሞ የእነዚህ ሃይሎች ዓላማ ምን እንደሆነ መንግስት ሳይረዳው በመቅረቱ አይደለም– ዴሞክራሲያዊ እንደመሆኑ መጠን ለጥያቄዎቹ ቅድሚያ በመስጠቱ እንጂ። እናም ቀደም ሲል በቡድኑ ቀርበው የነበሩትን ሦስት ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ አዳምጦ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥቷቸዋል።

ይሁንና ለቀረቡት ጥያቄዎች መንግስት ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል ስል፣ ቡድኑ ባገኘው ይሁንታ ረክቷል ወይም እጁን ሰብስቦ ተቀምጧል ማለት እንዳልሆነ ውድ አንባቢዎቼ ልብ ሊሉት ይገባል። ምክንያቱም ቡድኑ ከመንግስት ጋር እደራደራለው ብሎ የተነሳባቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች እነዚህ ምላሽ የተሰጠባቸው ስላልሆኑ ነው። ቡድኑ ላቀረባቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ያግኝም፣ አያግኝም ምንም የሚደንቀው ጉዳይ አልነበረም። እንዲያውም ጥያቄዎቹ ሊመለሱ ባይችሉ ኖሮ፣ በሰበቡ ብጥብጥ ለማስነሳት እንደመልካም አጋጣሚ ለመጠቀም ፍላጎት ነበረው። ዳሩ ግን እንደገመተው ሳይሆን በመቅረቱ ለሌላ ተደራራቢ የፖለቲካ ጥያቄዎችና የኃይል እርምጃዎች ራሱን ማዘጋጀቱን ሊገፋበት ችሏል።

እነዚህ ሃይሎች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ሲያደርሱ የቆዩትም ሆኑ ለመንግስት ሲያቀርቡ የነበሯቸው መቋጫ ያልነበራቸው የፖለቲካ ጥያቄዎች በዚህች ሀገር ላይ ፅንፈኝነትንና አክራሪነትን ለማስፋፋት ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን በገሃድ ያረጋገጡበት ነው ማለት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ግን ሴራቸው ቀድሞ ቢታወቅም ቅሉ፣ መንግስት ‘ምናልባትም እነዚህ ወገኖች ከስህተታቸው ይታረማሉ’ በሚል ሆደ ሰፊነት እርምጃ ሊወስድባቸው አልፈለገም። እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስም በሙስሊሙ ህዝብም ይሁን መንግስት በኩል ታላቅ ትዕግስትና ብስለት የተሞላበት አካሄድ ተስተውሎ ቆይቷል።

ሆኖም አክራሪው ቡድን በማንኛውም መልኩ የሚያደርጋቸው የብጥብጥ ግፊቶች መንግስትም ሆነ ህዝበ ሙስሊሙ በተከተሏቸው የሰከኑ አካሄዶች እየተቀለበሱ መቀጠላቸው አልተዋጠለትም። ሃቁን ተገንዝቦ አካሄዱን ከመቀየር ይልቅ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። በነገራችን ላይ የዚህ ቡድን የተስፋ ቆራጭነት ጉዞ ጥቂት ቁጥር ላላቸው ተከታዮቹ ብቻ ሳይሆን፣ ኃይሉን በስውር በመደገፍ ሀገራችን ውስጥ ሁከት እንዲነግስ ፍላጎት ላላቸው የውጭ ፅንፈኛ ሃይሎችም ብርቱ ህመም ሆኗል። በመሆኑም እነዚህ ኃይሎች በሃይማኖት ስም የለበሱትን ካባ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አውልቀው ስውር ፍላጎታቸውን አደባባይ ለማውጣት ወደ ተገደዱበት ደረጃ ለመሸጋገር በቅተዋል።

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከርኩት እነዚህ ሃይሎች በእስልምና ስም መነገድን በተያያዙበት ወቅት ሙስሊሙ ማህበረሰብ የ”ሰደቃ” ስርዓቱን እንዳያከናውን ለማስገደድ ብርቱ ጥረት አድርገዋል።ይሁን እንጂ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተነጠሉና እርቃናቸውን በቀሩበት ወቅት ሲያወግዙትና ሊያጠፉት ጥረት ሲያደርጉ ወደ ነበረው ሃይማኖታዊ ስርዓት ለመመለስ ነው የተገደዱት። ለዚህም በተለያዩ ወቅቶች ለሁከት ራሳቸውን ሲያዘጋጁ ሰደቃ በማድረግ “አንድነት” በሚል በአወሊያ ትምህርት ቤት አከናውነውት የነበረው ዝግጅት፣ ቡድኑ ከመነጠሉ የተነሳ ወደ ከፋ ተስፋ መቁረጥ የተሸጋገረ መሆኑን በገሃድ የሚያረጋግጥ ዕውነታ ነው። “አንድነት” በሚል ያዘጋጁት ስብሰባ ደግሞ ቡድኑ ከሙስሊሙ ህዝብ ልዩነት አለኝ በሚል የተነጠለና ለዓመታትም አንድ አለመሆኑን ተቀብሎ ሲንቀሳቀስ የቆየ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ግና ቡድኑ አብሮት ድንጋይ የሚያወራውረውን ደጋፊ ለማሰባሰብ አንድነቱ ድንገት ቢታወሰውም ቅሉ፣ ስለ

ሰላም የሚሰብከውን እስልምና ተጋፍቶ ለወጣው ይህ ፅንፈኛ ኃይል "አንድ" መሆኑን ያረጋገጠለት ምዕመን አልተገኘም።

ታዲያ ሁኔታው በዚህ ቀጥሎ የቡድኑ አጀንዳ ሃይማኖታዊ ሳይሆን ዓይን ያወጣ ፖለቲካ መሆኑ  በአደባባይ እርቃኑን መታየቱ አይቀሬ ሆኗል። ግና እንዴት?–እውነታው እንዲህ የሚነበብ ነው። …እንደሚታወቀው አዲስ አበባ የሀገራችን ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ መዲናም ናት። በየጊዜው ታላላቅ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ እንዲሁም ክፍለ-አህጉራዊ ስብሰባዎችን ታስተናግዳለች። የዛሬ ዓመት ገደማ የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባን ማስተናገዷ ይታወሳል። ታዲያ በዚህ ወቅት እነዚህ ሃይሎች የሀገርንና የህዝብን ሰላም ለማደፍረስ ብሎም በእንግዳ ተቀባይነትና በሰላምና ፀጥታ በኩል ህዝባችን የገነባውን መልካም ስም ለማደብዘዝ ያለመ የሁከት እንቅስቃሴን ለማካሄድ ነበር ቆርጠው የተነሱት። ለዚህም ደግሞ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ አባላቶቻቸውን "ስብሰባ እናካሂዳለን" በሚል ስም የጠሩበት ሁኔታ ነበር። ጥቂት ስራ አጥ ወጣቶችንም የውሎ አበል እየከፈሉ ለማሰለፍም ሙከራ አድርገዋል።

ከሌሎች አካባቢዎች ለመጡ ተከታዮቻቸውና ከጎናቸው ላሰለፏቸው ጥቂት ስራ አጥ ወጣቶች በቀን እስከ ሦስት መቶ ብር የሚደርስ የውሎ አበል የከፈሉ ሲሆን፤ ይህንንም ቡድኑ ብጥብጥ እንዲያካሂድ በድብቅ ድጋፍ ያደርጉለት ከነበሩ የውጭ ሃይሎች ስፖንሰር የተደረገ መሆኑ በመረጃ ሊረጋገጥ ችሏል። ነገሩ "ታሪክ ራሱን ይደግማል" እንዲሉት ዓይነት ሆኖ ነው መሰል በቅርቡም ሀገራችን በተመሳሳይ መንገድ የአፍሪካ ድርጅትን/ህብረትን 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ ውልደተ-ዕለትን ለማክበር እንግዶቿን ለመቀበል ሽርጉድ በምትልበት ወቅት ከከሸፈው የቀለም አብዮት አራማጁ ሰማያዊ ፓርቲ ጋር በመሆን በህብረቱ አዳራሽ ፊት 'ማቅ ለብሰን ማቅ መስለን ካልተገኘን ሞተን እንገኛለን' ሲሉም ተመልክተናቸዋል።

ይሁንና በዚህ መልኩ የሀገርን ገፅታ ጥላሸት ለመቀባት የተነሱት አክራሪ ፖለቲከኞች የሁከት እንቅስቃሴያቸውን ባሰቡት መልኩ ሊያካሄዱ አልቻሉም። በአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ዋዜማ ላይ ለማስነሳት ያሰቡት ሁከት በተለይም ከሰላማዊው የሙስሊም ማህበረሰብ

ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል። አብዛኛው ህዝበ-ሙስሊም "ሃይማኖታችን የፅንፈኞች መጠቀሚያ ሊሆን አይችልም" ብሎ በመረባረቡ ነው።

እርግጥ አክራሪዎቹ አምና በአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ወቅት የከሸፈባቸውን የሁከት እንቅስቃሴ በታላቁ የረመዳን ፆም መግቢያ ወቅት ለመድገም ነበር የተረባረቡት። በወቅቱ ዋነኛ ግባቸው በታላቁ አንዋር መስጂድ ላይ አድርገው የነበረ ሲሆን፤ በመርካቶ አካባቢም ትርምስን ፈጥረዋል። ወደ ታላቁ አንዋር መስጂድ በሃይል ገብተው ለፀሎት የተሰባሰበውን ህዝብ አግተዋል፣ ሃይማኖታዊ ስርዓቱን ከማወካቸውም ባሻገር ስርዓቱን የሚመሩ የተከበሩ ኢማሞችን ደብድበዋል፣ ድምፅ ማጉያዎችንና ጄኔሬተሮችን ተቆልፈውባቸው ከሚገኙ ክፍሎች ሰብረው በማውጣት የጅሃድ ጦርነት ቅስቀሳ አካሂደዋል፤ ጥሪያቸውን በማይቀበሉት ላይም ዛቻንና ድብደባን ሰንዝረዋል።

በዘንድሮው የህብረቱ 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ላይ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር በመቀናጀት ለመከወን ያሰቡት ፀረ-ህገር ተግባር በአብዛኛው ሙስሊም እምቢታ ምክንያት ስላልተሳካላቸውም፤ ልክ እንደ አምናው አሁን ባለንበት በቅዱሱ የረመዳን ፆም ወቅት በአንዋርና በቤኒን መሳጂዶች ውስጥ የሀገርን ኩራት በማቃለል ጭምር ሁከትን ለመፍጠር ችለዋል። ታዲያ ይህን ሁሉ የአክራሪዎችን ድርጊት አብዛኛው ሰላማዊ ሙስሊም ምዕመን 'የእናንተ መንገድ አያስኬደንም፣ እኛ ሰላምን እንጂ ሁከትን አንሻም' እያለ መታገል በራሱ ጊዜ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። ግና መንግስት የአክራሪዎቹን ያልተገቡ ጥያቄዎችን እንኳን ምላሽ በመስጠት ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን ለማክበር ጥረት ሲያደርግ፤ አብዛኛውን ሰላማዊ ሙስሊም ያለ ሁከት የመስገድና አላህን የመለመን ስርዓቱን የማከናወን ህገ-መንግስታዊ መብቱን ለምን እንደማያስከብርለት ለእኔ ግልፅ አይደለም። በህዝበ-ሙስሊሙ ይሁንታ የተመረጠው መጅሊስም ቢሆን ሁኔታውን እንደ ባዕድ ቁጭ ብሎ ከመመልከት ይልቅ፤ ይህን በአክራሪዎች እየተጣሰብን ያለውን መብት ለምን እንደማያስከብርልን እንደ አንድ ሙስሊም መጠየቅ የግድ ይለኛል።

እርግጥ መንግስት በተለያዩ ወቅቶች በእነዚህ በውጭ ሃይሎች ምንዳ በተንቀሳቀሱት ጥቂት አክራሪዎችና መሪዎቻቸውን የጥፋት አጀንዳ ለህዝብ በይፋ ከማሳወቅ አልፎ፣ ከመላው ሰላም ወዳዱ ህብረተሰብ ጋር በመተባበር የአክራሪዎቹን መረን የለቀቀ ህገ- ወጥ

አካሄድ ለመቆጣጠር ያስቻሉ ተከታታይ እርምጃዎችን ያለ አንዳች መብት መሸራረፍ መውሰዱ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። እነዚህ በውጭ ኃይሎች ገንዘብ የታወሩ ጥቂት የወሃቢ/የሰለፊ ፅንፈኞች፣ ዜጎች መንፈሳዊ ተግባራት በሚያከናውኑባቸው መስጂዶችና የፀሎት ስፍራዎች የሽብር አድማዎችን በመጠንሰስና በሀገር ሰላምና ፀጥታ እንዲሁም በሰላማዊ ዜጎችና ምዕመናን ላይ አስከፊ የወንጀል ጥቃቶችን ለመፈፀም ሲያሴሩ ተገኝተው ህጋዊ እርምጃ የወሰደባቸው መሆኑም የሚታበይ አይደለም፡፡ እነዚህ ተግባራቱም በሁሉም ሰላም ወዳድ ማህበረሰብ በተለይም በአብዛኛው ሙስሊም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና ‘ይበል’ የሚያሰኙ ናቸው።

ይሁንና በእኔ እምነት መንግስት የሰላማዊውን ሙስሊም መብት አሁን እያስከበረ ካለው በተሻለ ሁኔታ ማስከበር ይኖርበታል። ምክንያቴ ደግሞ ሁለት ናቸው። አንደኛው መንግስት በህገ-መንግስቱ ላይ የሰፈረውን የዜጎችን የእምነት ነፃነትና የአምልኮ እኩልነትን የማረጋገጥ ኃላፊነትና ግዴታ ያለበት በመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አክራሪዎቹ ባለፈው ጁምዓ ሁከት ለመፍጠር በተለያዩ ዘመናዊ የመገናኛ አውታሮች በፀሎት ስፍራዎች ተጠራርተው ሲያበቁ፣ ኋላ ላይ በረመዳን ፆም ፍቺ ላይ ሁከት ለመፍጠር መቀጣጠራቸው ስለሚያሳስበኝ ነው። በመሆኑም መንግስት በአንድ መልኩ እጅግ በበዛ ትዕግስት የአክራሪዎቹን የእምነት ነፃነትን በማክበር፣ በሌላ መልኩ ደግሞ ወንጀል የፈፀሙ አባሎቻቸውን ለህግ በማቅረብ የእነዚህን ኃይሎች ህገ-መንግስታዊ መብት እያስከበረ እንደመጣው ሁሉ፣ የአብዛኛውን ሰላማዊ ሙስሊም ያለ ሁከት በሰላም ፀሎቱን ለአላህ የሚያቀርብበትን መብት ከፀረ-ሰላም ኃይሎች ይበልጥ በመከላከል ማስከበር አለበት ባይ ነኝ። ምክንያቱም አርብ በመጣ ቁጥር ለአላህ የምናቀርበው ፀሎት በሁከት ናፋቂዎች መደናቀፍ ስለሌለበት ነው። ዕውን እስከ መቼ አርብ በመጣ ቁጥር ፀሎታችን እየተስተጓጎለ ይቀጥል ይሆን?–አዎ! የዚህን ጥያቄዬ ምላሽ እንደ ዜጋና እንደ አንድ ሙስሊም ምዕመን ለመንግስት እንዲሁም ክሰተቶቹን በዝምታ እየተመለከተ ላለው መጅሊስ የምተወው ይሆናል።

እንደሚታወቀው አክራሪዎቹ ህገ-ወጥ የሽብር ተግባሮቻቸውን የሚቃወሙ ምዕመናንና የሃይማኖት አባቶችን ስም የያዘ ዝርዝርን እስከማዘጋጀትም በመድረስ በህብረተሰቡ ሰላማዊ ፀጥታ ላይ የተጋረጡ አደገኛ አሸባሪዎች መሆናቸውን በይፋ ያረጋገጡ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈም ግልፅ ፀረ-መንግስት መፈክሮች እና ፖለቲካዊ

የተቃውሞ ውርጅብኞችን እያሰሙ የፀሎት ስርዓቶችን በማወክና በመበጥበጥ በዜጎች ላይ ከፍተኛ እንግልት ያደረሱ መሆናቸውም እንዲሁ፡፡

እንግዲህ እነዚህ ፅንፈኞች ናቸው በውጭ ሃይሎች የገንዘብ ድጋፍ እየታገዙ በረመዳን ፆም ፍቺ ላይ እንደ ቅዱስ ተግባር ሁከት ለመፍጠር የተቀጣጠሩት። ቅዱሱ የረመዳን ፆም ሊፈፀም ደግሞ የቀሩት ቀናት በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ናቸው። እነዚህ አክራሪዎች ከአንድ ዓመት በላይ አርብ በመጣ ቁጥር በየመስጂዱ ያለ ፈቃዳችን እየተገኙ ፀሎታችንንና ፆማችንን በሁከት ተግባራቸው ሲያራክሱብን ቆይተዋል። አሁን ግን ይህ ዕድል በፍፁም ሊሰጣቸው አይገባም። በሰላም ፆመን አላህ ለዚያች ቀን በሚያበቃን የፆም ፍቺያችንን ቀን ከሁከት በፀዳ መልኩ ማክበር እንፈልጋለን። እናም መንግስት ሰላማዊ የሆነው አብዛኛው ሙስሊም በሰላም በዓሉን የማክበር ህገ-መንግስታዊ መብታችንን ይበልጥ ሊያስከብርልን ይገባል። በአብዛኛው ህዝበ-ሙስሊም ሙሉ ይሁንታ የተመረጠው መጅሊስም የምዕመኑን ወክሎ የሚንቀሳቀስ እንደመሆኑ መጠን ችግሮቻችንን እያየ ዝም ከማለት ይልቅ፤ይህን ጥሪያችንን ማዳመጥ ይኖርበታል። አዳምጦም ለተግባራዊ እርምጃ መነሳሳት አለበት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰላም ወዳዱ ሙስሊም ምዕመን እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ በአክራሪዎች ፖለቲካዊ ሴራ ሳይዘናጋ የጀመረውን የታላቁን ረመዳን ፆም በፍፁም ሰላምና ደስታ እየከወነ፣ በፍቺውም ወቅት ሁከት የሚያራምዱ ፅንፈኛ ምንደኞችን እንደተለመደው ከውስጡ በማንጓለል ለፀጥታ ኃይሎች አሳልፎ በመስጠት ሰላሙን በእጁ መጎናፀፍ ይኖርበታል ባይ ነኝ። እስቲ ለማንኛውም አላህ የዚያ ሰው ይበለን። ረመዳን ከሪም!